የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.2
ADDIS ABABA 5th December, 2014

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯ ዓ.ም

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............ገጽ ፯ሺ፯፻፶፪

CNTENTS

Regulation No. 326/2014

Industrial Parks Development Corporation Establishment Council of Ministers Regulation……………........Page 7752

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯

## የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ አንቀጽ ፴፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. መቋቋም

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽኑ" እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 326/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE INDUSTRIAL PARKS DEVELOPMENT CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010, Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No.25/1992 and Article 35(1) of the Investment Proclamation No. 769/2012.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Industrial Parks Development Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 326/2014".

### 2. Establishment

1/ The Industrial Parks Development Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a federal government public enterprise.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price ብር 6.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

**፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

**፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተቋቋሙባቸው ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

**፭. <u>ዓላማ</u>**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማልማት፣የማስተዳደር፣የለማ ቦታ በሊዝ ማከራየት እና ግንባታዎችን የማከራየት ወይም በሽያጭ የማስተላለፍ፤

፪/ የአገራዊ ስፓሻል ማስተር ፕላንን መሠረት በማድረግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ዝርዝር ማስተር ፕላን የማዘጋጀት እና ከክልል መንግሥታት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት መሬት በመረከብ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት መሬት ባንክ ሆኖ የማገልገል፤

፫/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች ለኢንዱስትሪ ፓርኮች አልሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ፤

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስተዳደር ተግባር በሥራ አመራር ውል ለሌሎች አካላት የማስተላለፍ፤

፭/ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጠቀሜታ በሠፊው በማስተዋወቅ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሠማሩ ባለሀብቶችን የመሳብ፤

፮/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ እና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ የመሸጥና በዋስትና

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. <u>Supervising Authority</u>**

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the Corporation.

**4. <u>Head Office</u>**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices in areas where industrial parks are established.

**5. <u>Purpose</u>**

The purposes for which the Corporation is established shall be:

1/ to develop and administer industrial parks, lease developed land and lease or transfer, through sale, constructions thereon;

2/ to prepare detail national industrial parks master plan based on the national special master plan and receive land and serve as industrial park land bank in accordance with agreement concluded with regional governments;

3/ in collaboration with the concerned bodies, to make necessary infrastructure accessible to industrial park developers';

4/ to outsource, through management contracts, when it deems necessary, the management of industrial parks;

5/ to promote extensively the benefits of industrial parks, and thereby attract investors to the parks;

6/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge

የማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል የመደራደርና የመፈራረም፤

፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን የማካሄድ፡፡

**፮. ካፒታል**

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፲ ቢሊዮን (አሥር ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

**፯. ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፰. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፱. የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፯/፪ሺ፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፯/፪ሺ፭ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ኮርፖሬሽን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

**፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

7/ engage in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

**6. Capital**

The authorized capital of the Corporation is Birr 10,000,000,000 (Ten Billion Birr) of which Birr 2,500,000,000 (Two Billion Five Hundred Million Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. Liability**

The Corporation may not be liable beyond its total assets.

**8. Duration of the Corporation**

The Corporation is established for an indefinite duration.

**9. Repealed Regulation**

The Ethiopian Industrial Development Zones Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 297/2013 is hereby repealed.

**10. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopian Industrial Development Zones Corporation Established under the Council of Ministers Regulation No. 297/2013 are hereby transferred to the Corporation.

**11. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of December, 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.2
ADDIS ABABA 5th December, 2014


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯ ዓ.ም

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............ገጽ ፯ሺ፯፻፶፪


**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯**

**የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ አንቀጽ ፴፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽኑ" እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**CNTENTS**


Regulation No. 326/2014

Industrial Parks Development Corporation Establishment Council of Ministers Regulation.........................Page 7752


**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 326/2014**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE INDUSTRIAL PARKS DEVELOPMENT CORPORATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010, Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No.25/1992 and Article 35(1) of the Investment Proclamation No. 769/2012.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Industrial Parks Development Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 326/2014".

2. **Establishment**

1/ The Industrial Parks Development Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a federal government public enterprise.